# ሁለተኛው ዙር የትሮይ ፈረስ

ሳሙኤል ሽፈራው/ዳላስ

የትሮይ ፈረስን ተምሳሌነቱ ለምን እንደሆነ ሁሉም ይገነዘበው ይመስለኛል። ሆኖም በእኛ አገር ሲተረጎም ግን በትክክል ከምሳሌነት ባለፈ የተተገበረ ለመሆኑ ያለፉት 20 አመታት አሳይተውናል። ነገሩ እንዲህ ይጀምራል። እስፓርታውያን ጠላቶቻቸውን አምላክ አባረረልን በማለት በደጃፍ ያገኙትን የእንጨት ፈረስ ከአምላክ የተላከ ስጦታ ብለው በማመን እየገፉ ወደመሐል መንደራቸው በማስገባታቸው ላልገመቱት ጥፋት ተዳርገዋል። ጠላቶቻቸው የትሮይ ሰወች ከእንጨት በተሰራ የፈረስ ሆድ ተሸሽገው በመግባት በእኩለ ለሊት ከተደበቁበት ወጥተው  የትሮያን ወታደሮችን ወደ እስፓርታ ከተማ በማስገባት፤ በቀን ጦርነት ያልቻሉትን የእስፓርታ ወታደር በውድቅት ለሊት ፈተውት አደሩ። ይህ አፈታሪክ ከዘመን ዘመን በምሳሌነት ሲነገር ኖረ።

ዛሬ ይህን የትሮይ ፈረስ ተምሳሌነቱን ለማንሳት ያስገደደኝ አገራችን በመልክአ ምድር አቀማመጥና ተፈጥሮ በለገሳት የአየር ጸባይ ከተወላጆቿ ነጥቀው ለመውሰድ ስልጣኔ ከጀመረበት ዘመን ጀምረው ሞክረዋታል። ሆኖም ግን በተጋድሎ ሳይሳካላቸው እስከአለንበት ዘመን አንዴ የቆዳ ስፋቷ ሲጠብ ሌላ ጊዜ መልሳ ወደነበረችበት ስትደርስ እስከ ዚህ ዘመን ዘልቀናል። አንድ አባባል አለ፤ አገሮች ቋሚ ጥቅም እንጅ ቋሚ ጠላትና፤ ወዳጅ ሊኖራቸው አይችልም ይባላል። ይህ አባባል ለብዙ አገራት እውነት ሊሆን ይችላል። እውነት ነውም። ለምሳሌ ዩኤስ አሜሪካንን ብንወስድ ጥቅሟን ብትችል በሰላም ካልሆነ ግን በሀይል ስታስጠብቅ ተመልክተናል። ባገራችን የቀዳማዊ ሐይለስላሴ መንግስት በ1966 ቱ አብዮት ተፈንቅሎ በምትክ ወታደራዊው ደርግ ስልጣን ሲይዝ፤ ኢትዮጵያ የድሮ ወዳጅ ናት ሳትል ጦር ጭና ለጎረቤታችን ሶማሊያ በመስጠት ዳር ድንበራችንን አስደፍራ ነበር። መንግስታችን ገንዘብ አውጥቶ የገዛውን የጦር መሳሪያ በመከልከልም ለጥቃት አጋልጣናለች። ይህ እንግዲህ በአገር ጥቅም ይሉንታና ወዳጅነት የሚባል እንደሌለ የሚያሳይ ጉዳይ ሲሆን፤ ቋሚ ወዳጅም ሆነ ቋሚ ጠላት የለም ለሚለው አባባል መልስ ሰጭ ነው። ሆኖም አገራችንን አስመልክቶ ግን ይህ አባባል ሊሰራ አይችልም። ኢትዮጵያ ዘመን ከተፈጠረ ጀምሮ ቋሚ ጠላት ያላት አገር ናት። በጠላቶቻችን ታስቦ ይህች አገር መኖር የለባትም ወይንም በእነሱ ግዛት ስር መጠቃለልና ያሻቸውን ሊያደርጉ ይመኟታል። ኢትዮጵያ ተፈጥሮ በለገሳት አቀማመጥና ውበት የሚቀኑባት በባላንጣነት ፈርጀው ጊዜ የማይሽረው ክፉ ተግባር ሲሰሩባት ኖረዋል። የኦቶማን ቱርክ ሐያል መንግስት በመካከለኛው ዘመን በተደጋጋሚ ይህችን አገር የቅኝ ግዛት ለማድረግ ሕዝቧንም በራሱ ባህል፣ ቋንቋና ልማድ ለመቀየር ብዙ ሙከራ አድርጎ ሳይሳካለት ቀርቷል። ከሙከራወቹም አንዱ የትሮይ ፈረስ አርጎ ያዘመተው መሐመድ ግራኝ ታሪክ አንድ አቢይ ምሳሌ ነው።

አገራችንን ለመንጠቅ የከጀሉ ሁሉ ጠላቶች የእግር መርገጫ የሚያገኙት ተወላጅ ዜጎችን በመመልመልና ፈታውራሪ በማድረግ ነበር። በ18ኛው መቶ የመጨረሻ አመታት ግብጾችና ቱርኮች በተደጋጋሚ ሞክረው ያልሆነላቸውን የቀይ ባሕርን የነሱ የማድረግ ጽኑ አላማ፣ የአውሮፓዋ ጥሊያን በእንግሊዝ ገፋፊነትና ድጋፍ ተነሳስታ ምጽዋን ለመቆጣጠር ችላለች። ታዲያ ምጽዋንና አሰብን ለመያዝ የተጠቀመችው የአካባቢ ባላባትን በመደለልና በገንዘብ በማባበል ነበር። ያ ጠንቅ እስከዚህኛው ዘመን ዘልቆ ሌሎች የትሮይ ፈረሶች አገራችንን ያለባሕር በር አስቀርተዋታል።

ከታሪክ እንደምንረዳው ይህ የዛሬው ድርጊት፤ የዚህችን አገር አንጡራ ሀብት ነጥቆ ሌላና ያልነበረች መንግስት መፍጠር ጊዜአዊና ሌላ የታሪክ ገጠመኝ እንጅ፤ እስከወዲያኛው የሚዘልቅ እንደማይሆን ነው። በ1991 ዓ.ም በወያኔ፣ ሻብያ፣ ሱዳን፣ ብሎም ኦነግ የተደረገው መሐከላዊ መንግስትን የማፍረስ ተግባር በከፊል ግቡን መትቶ ኢትዮጵያ ቅርጿን ቀይራ አንድ የሰሜን ግዛቷ ስትገነጠል። ቀሪውን በዘር ክልል በመሸንሸን፣ የተረጋጋችና አንድ ህልውናዋን ጠብቃ የምትቀጥል ሉዓላዊት አገር እንዳትሆን በደነገጉት አዲስ ሕገመንግስት ያገሪቱ አንድ አካል ባሻውና በፈለገው ጊዜ እንደተገነጠለችው ኤርትርያ እንዲሆን መብት በሚል ሰፍሮለታል። እነዚህ የትሮይ ፈረሶች መንበረ ስልጣኑ ላይ በተቀመጡባት አገር እንደ አንድ የባእድ ቅኝ ገዥ ሐይል ይህ ለኛ አይገባም በማለት በግዜው የተባበሩት መንግስታት ዋና ጸሐፊ ለነበሩት፤ ለአገራችን ታሪካዊ ጠላት ቡትረስ ቡትረስ ጋሊ ደብዳቤ በመጻፍ የራስን አገር በማስገንጠል በአለም ላይ የመጀመሪያው መሪ ሆነዋል።

ለነመለስ ሕወሐት ለትግራይ ሕዝብ ነው የተነሳነው ለሚሉት አሰብን አሳልፎ መስጠት ሚስጥሩ ለብዙ ወገኖች እስካሁን ግልጽ አይደለም። ምክንያቱም ድሮም ቢሆን አሰብና ምጽዋ ለደቡባዊው፣ ለምስራቅና መሐል አገራችን ብዙም ግልጋሎት እንዳልነበረው ስንረዳ፣ ለትግራይና ምናልባትም ሶስት የሰሜን ክፍለ ሐገራት ሊያገለግል የሚችለውን የባህር በር ነበር አይገባንም በማለት የሰጡ። እነዚህ የትሮይ ፈረሶች ዛሬ ድረስ ለኤርትራ ሏላዊነት ከሻብያ በላይ ተቆርቋሪ ሆነው ሲናገሩ ይደመጣል። የስብሐት ነጋን የአሜሪካን ድምጽ ሬዲዮ ቃለምልልስ ያስታውሷል። በስልጣን ላይ እንዳሉት የሕወሐት መሪወች ሁሉ በመገንጠል ላይ ተንተርሰው የተነሱ ድርጅቶች ላለፉት 40 አመታት እንዳስተማረን ከሚቀናቀኑት በላይ ቆምንለት የሚሉትን ሕዝብ እንደሚጎዱ ሻቢያና ወያኔ ቋሚ ምስክር ናቸው። ወያኔ የኢትዮጵያ ቁንጮ የሆነውን የትግራይን ሕዝብ መገንጠል የማይችሉ ሆነው ሲያገኙት፣ ምርጫቸው የትሮይ ፈረስ ሆነው ሻብያን ከወደቀበት ጎትተው አገር ገንጥለው ማስረከባቸው፣ ከሁሉም በላይ ጉዳት ያደረሱት በድንበረኛው የትግራይ ወገናችን ላይ ነበር።

**ዛሬስ ምን እየተሰራ ነው?**

መቸም ታሪክ እራሷን አትደግምም የሚል አባባል ነበር። አሁን አሁን ባገራችን ታሪክ ሙቶ ጊዜ እራሷን ስትደግም በማየታችን የአባባሉን ሳይንሳዊነት እንድንጠራጠር ሳያደርግ አልቀረም።

ነገሩ እንዲህ ነው። የወያኔ የሻብያ፣ ኦነግ ድራማን ባየን ድፍን 20 አመት ዳግም ያን ጊዜ ለመድገም ሲሞከር እያስተዋልን ነው። ትዝ ይላችሁ ይሆናል። በ1991 ዓ.ም አሜሪካኖችና እንግሊዞች በኢትዮጵያ ሕዝብ ጀርባ ፍርድ ጥለው ሎንደን ላይ የአንድነት ደጋፊ ሐይላትን አስወግደው ግንጠላን ዋነኛ አላማ አርገው የቆሙ የጎሳ ድርጅቶችን ሰባስበው በአፍሪካ የአሜሪካ ዋና ዲፕሎማት በነበሩት ሔርማን ኮሀን አማካኝነት አገራችንን አስረከቡ። የዚህ ሚስጢር ብዙ ድብቅ አልነበረም። በደርግና ባላቋረጠ በፔትሮ ዶላር ፋይናንስ በተደረገ ጦርነት ለአገሩ አንድነት ሲታገል ሀብት ንብረቱን እስከወለዳቸው ልጆቹ የተነጠቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአምላኩ ነግሮ ዝም ከማለት ውጭ ያነን ታላቅና ከባድ ሴራ ሊጋፋ የሚችል ተከሻ አልነበረውም።

ዛሬ ዳግም ተመሳሳይ የውጭ ሐይሎች የዘየዱት የሚመስል ዳግም ጥፋት መሽተት ጀምሯል። አሁንም ለሁለተኛ ጊዜ የኦሮሞ ነጻነት ግንባርን አዝለው ሊያስገቡ የሚመስል ነገር እያየን ነው። ግለሰቦች እንበላቸው ወይንም ድርጅት ይባሉ በቨርጅኒያ በጁላይ 10 ቀ 2011 በተደረገው ስብሰባ ዶክተር ኑሩ ደደፋው ከዚህ በፊት በኦሮሞ ነጻነት ግንባር ከሚሰጡ ጸረ ኢትዮጵያ ሐሳቦች የተለየ አዲስ መርዶ አልተናገሩም። በግራና በቀኝ ያጀቧቸው ሁለቱ ምሁራን በእውነት ኢትዮጵያንና የአገር አንድነትን የሚጠቅም ስራ ነው ብለው አምነውበት ነው ወይንስ በሌላ ተቦክቶ ባለቀ አስፈጻሚ ሊሆኑ የሚለውና፤ ከሁሉም በላይ ድፍን ኢትዮጵያውያን የማያውቁት ለነዚህ ግለሰቦች የተገለጸ ነገር አለ? የሚለው ሁነኛ የሁላችንም ጥያቄ ነው።

በሌላ በኩል ሁለቱም ዶክተር ኑሩን አጅበው የተገኙ ምሁራን ከአሲምባ እስከ አለንበት ወቅት ሰፊ የታሪክ ሰንሰለት ያላቸው ስለሆነ፣ ለዚያም መቸስ ያልሞተ ሰው ይባል አይደል፤ አንደኛው ምሁር ምንስ ቢሆን በምርጫ 97 ተሳትፈው ሰላም በአሜሪካኖች ይገኛል፣ የኢትዮጵያን ችግር በሰላም ይፈቱልናል ብለው በማሰብ ይመስላል አለያም የኢኮኖምክስ ጠበብት ስለሆኑ ከጥቅሙ ጉዳቱ ሊያመዝን ይችላል ብለው አስበውም ሊሆን ይችላል   የተጠራውን የሙት ከተማ አድማ እንዳይደረግ በአሜሪካኖች አማላጅነት አስቁመው፤ ለዚያም ሁለት አመት በእስር መከራቸውን በማየት ከፈሉበት የሚሉ አሉ።

ሌላው ምሁር ዶክተር ጌታቸው በጋሻው በእርግጥም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ጀምረው እስከአለንበት ጊዜ ብቅ ጥልቅ እያሉ ከንቅናቄ ተለይተው አያውቁም ይላሉ የሚያውቋቸው የቅርብ ጓደኝነታቸው። እኒህ ግለሰብን ሰፋ ያለ ትችት የሚያቀርቡባቸው አብረዋቸው የታገሉት ሲሆኑ፤ በምሬት የሚያቀርቡት ጌታቸው ብዙ እድል ተሰጥቶት መልካም ውጤት ከማስመዝገብ ይልቅ በቆመበት ሁሉ ፍርሻንና መለያየትን ፈጥሮ እንደሚለይ ይናገራሉ። ከቅርብ ጊዘ ትውስታቸው የሚጀምሩት በቅርብ የሚያውቋቸው ግለሰቦች፤ በ2004 ወደድሮ ድርጅታቸው ተመልሰው በዚያው አመት በተጠራ የፓርቲው አራተኛ ጉባኤ የአመራር አባል ሆነው መመረጣቸውን ይዘከሩና፤ ግለሰቡ ወደ አመራር ከተቀላቀሉ ጀምሮ የነበሩ በውይይት ሊፈቱ ይችሉ የነበርን ቅራኔ ማራገብ ስራየ ብለው በመያዝ በኋላም ለተከሰተው ድርጅቱ ለሁለት የመከፈል አደጋ ዋናው አሽከርካሪ ነበሩ ይባላሉ። የዶክተሩን ጉዳይ በዚህ አይቋጩም። በ1979-80 እ.ኤ.አ የኢሕአሰን ሰራዊ ተሳክቶላቸው የበተኑ ግለሰቦች ጋር የተባበሩ እንደነበርም ያወሳሉ። ለዚህ እንደማስረጃ የሚያቀርቡት፤ የሁለተኛውን ሪጅናል ሰራዊት ገፍተው ሽንፋን ካሻገሩ በኋላ አምራኮባ ሰፍሮ ለመመለስ በተስፋ ላይ የነበረውን ሰራዊት ወክለው እያለ ውክልናቸውን ትተው ሰራዊቱ ተስፋ ቆርጦ እንዲበተን አድርገዋል በማለት የጥፋት ወንጀላቸውን ያባዙታል። ጉድና ጅራት ወደኋላ ነው እንደሚባለው ዶክተር ጌታቸው በቅርቡ ከፍለውት ከወጡት አንደኛው አካልም በአመራር ተቀምጠው ለመምራት ሳይሆን የኦሮሞ ነጻነት ግንባርን ድርጅቱ እንዲቀበል የእጅ ጥምዘዛ ሲጀምሩ ለዘመናት በትግሉ ጎራ የቆዩት አይሆንም በማለታቸውና፣ እርሳቸውም ኢ.ነ.ግን ያልጨመረ ትግል ዋጋ የለውም በማለት አመላቸው ከፍቶ አመራሩን እንደ አፍላ ጎረምሳ በማመሳቸው ከአመራር እንዲገለሉ ተደርጓል። በዚያ ሳያቆሙ ድርጅቴ ነው በማለት እስከ መሪነት የደረሱበትን ድርጅት ከቀይ ሽብር በኋላ አልቀጠለም እኮ እስከማለትም ደርሰዋል። "አዲዮስ ኢሕአፓ" በሚለው ዝነኛ መጣጥፋቸው ዶክተር ጌታቸው አጀብ ያሰኘ አስተያየቶችን ለግሰውናል። ለምሳሌ በዚሁ በ ፌብሯሪ 20 ቀን 2010 እ.ኤ.አ በጻፉት መልእክት እንዲህ ብለው ነበር።

<u>***"ሁሉንም ሀሳቦቹን እጋራለሁ ለማለት ሳይሆን፣ ሚቹ አቶ ዘርዑ ክሸን፣ ከተማ ውስጥ ከተመታን በኋላ ኢሕአፓ የሚባል ነገር እኮ የለም ብሎ ነበር አንድ ጊዜ። ይህም በወቅቱ አነጋግሮናል። ሆኖም ግን፣ በከተማ ውስጥ ሙሉ በሙሉ መመታታችንንና በየእርከኑ  የነበሩትን በርካታ የአመራር አባላትና የሰው ኃይላችንን እንደገበርን እያወቅን፣ የሕዝባችንን ችግር በመመልከት፣ በአገሪቱም ላይ ያንዣበቡትን አደጋዎች በማሰብና፣ ለትግሉም የተከፈለውን መስዋዕትነት በመገንዘብ እስቲ እንደምንም እያልን እንሞክረው ብለን በሠራዊቱ ውስጥ ችግር እስከተነሳበት ጊዜ ድረስ (ማለትም ብተና ተብሎ***</u>

እስከሚጠራው ጊዜ ድረስ ማለት ነው) በድርጅቱ ስም ስንቀሳቀስ ነበር።”

ከላይ ባለው አበባል ስንሄድ አንድም ከአንድ እሳቸውን ከመሰለ ምሁር ያውም በህይወት የሌለ ሰውን ጠቅሰው፤ ደግሞም የጽሁፍ ማስረጃ በሌለው በአፍ ተባለ በሚል በእርግጥም ግለሰቡ የታገሉና መስዋእትነት የከፈሉ። በህይወት በኖሩበትም የታገሉበትንና የመሩትን ድርጅት አካፍተው ያቀረቡበት ጊዜ ካለመኖሩ ባሻገር፣ ከትግል ለመሰናበታቸውም ቢሆን የጤና ጉዳይ እንደነበር በጊዜ የሰማነው ነው። ዶክተር ጌታቸው ከብዙ አመታት በኋላ ተመልሰው እስከመሪነት ደርሰው ቃል ገብተው የመሩትን ድርጅት ከሰላሳ አመት በፊት ነዉ የጠፋው ሲሉ ምን ማለት እንደፈለጉ ለአንባቢ ግምት እንዲወስድ በሚል እዚህ ላይ አቀረብሁት። እንዴው ነገርን ነገር ያነሳዋል ስለሆነ ያንድን ሰው ስነ ባሕርይ መማሩ ሳይሆን ተግባራቱ ገላጭ ሰለሚሆን ያንን ለአንባቢ ለማሳየት የቀረበ ከሳቸው ጽሁፍ “አዲዮስ ኢሕአፓ” ከተሰኘው የተወሰደ ነው። በጽሁፋቸው አዲዮስ ኢሕአፓ (ደህና ሰንብት ኢሕአፓ እንደማለት ሲሆን) ይሉና፣ ኢሕአፓ የለም አልነበረም ማለታቸው እርስ በእርሱ የሚጋጭ ነውና ጽሁፋቸውን ያነበቡ ግራ መጋባታቸውን ይናገራሉ።

ዛሬስ እኒህ ምሁር ምን እየሰሩ ነው? በሰሞኑ የቨርጅኒያ ሦስትዮሽ ስብሰባ በግራና በቀኝ የታጀቡት የኦሮሞ ነጻነት ግንባር አመራር አባል ደግመው ያስረገጡት ነገር ቢኖር፤ ሻብያ ኤርትራን በሐይል ከመቆጣተሩ በፊት ይል የነበረውን ሕዝበ ውሳኔ እናሰጣለን ነው። የሻብያውም ሆነ የኢ.ነ.ጉ ሕዝበ ውሳኔ ማለት ደግሞ ለአፍ እንጅ በተግባር ዴሞክራሲያዊ ባልሆነ የፕሮፓጋንዳና የጥላቻ የመለየት አፈጻጸም ማለት ነው። ዶክተር ጌታቸው አዲዮስ ኢሕአፓ ያሰኛቸውም በመሪነት ተቀምጠው በነበረበት ጊዜ ከኦ.ነግ ጋር መስራት አለብን ብለው በመከራከራቸው፣ አይሆንም የሚል ምላሽ ሲያጋጥማቸው አመላቸው ከፍቶ፡ ከጎናቸው አብረው የነበሩትን የተለያየ ስም ሰጠው እንደተባረሩ የቅርብ ትውስታ ነው ይላሉ የሚያውቋቸው ወዳጆቻቸውና ያጭር ጊዜ ጓዶቻቸው። ታዲያ የቨርጅኒያው ስብሰባ ማንም ይደግፈው ማን ከጀርባው ይቁም፤ የነዚሁ ሁለት ወገኖቻችን የትግል ውጤት መሆኑ ነው። በእርግጠኝነትም የትም ላይ ቢቀመጡ ያልጣማቸው ዶክተር ይህን ቀን በማየታቸውና ከኦሮሞ ነጻነት ግንባር ጋር ይፋዊ ትሥራቸውን ባደባባይ ማውጣታቸው የናፈቁት ህልም እንደተፈታላቸው የሚቆጥሩ ይሆናል ብለው አንዳንድ ወዳጆቻቸው ታዝበዋል። ጠንከር ብለው በምሬት የሚተቿቸው ደግሞ፣ ጌታቸው የኢሕአፓን የመጨረሻ ማየት ይመኙ የነበረውና ድርጅቱን ካንድ ሁለትና ሦስት ጊዜ የታገለው (ድርጅቱን ለማጥፋት ማለት ነው) ይህችን ቀን በመመኘት ለብሔራዊ ትግል፣ ለአገር አንድነትና ሉአላዊነት ግንባራቸውን የማያጥፉ የዚያን ትውልድ ታጋዮች ባህርይ ጠንቅቀው ስለማኢያውቁ ነበር፤ ለማጥፋት መከራቸውን ያዩት ይላሉ።

ያም ሆነ ይህ ሕወሐት/ኢሕአዴግን በኦነግ ለመለውጥ ለምን ተፈለገ? ኢትዮጵያ የምትባል አገር እንዳትኖር ኦነግ ከሻብያና ከወያኔ ያነሰ ተዋጽኦ የለውም። እነዚህ ድርጅቶች በስም እንጅ የዚህችን አገር ጥፋት ለማምጣት በመረባረብ ባደረጉት ታሪካዊ ተጋድሎ አንድም ሶስትም ናቸው። ኤርትራን በማስገንጠል ኦነግም ተሳታፊ ነበር። የሽግግር ቻርተሩን በማውጣትም ሆነ፣ አጥፊውን ሕገመንግስት ተብየውን በማጽደቅ ከወያኔ ጋር የደከመ ነው። እንደሚባለው ከሆነ ኦነግ ያገኘውን ድል ያገኘ የለም የሚሉ ብዙ ናቸው። ቋንቋችንን ቁቤ በማድረግ፣ ወገኖቻችንን አልሆነም እንጅ ደም ለማቃባት በአሰቦት፣ በአርባ ጉጉና በወለጋ ሆሮ የሞከረው ከሻብያና ወያኔ የተናነሰ አልነበረም። አሁንም ቢሆን ያው እንደተናንቱ የአቢሲኒያ ቅኝ ተገዥ የሚለውን አልተወም። ወይም በድህረ ገጹ ያሰፈረውን የነጻ መውጣት ጥያቄ አልሰረዘም። እንዴውም እንደምናየው በአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮና በአትላንታ፣ አሁን ደግሞ በቨርጅኒያ አቋሙን ግልጽ አድርጓል። ለነገሩ ድርጅቱ ሳይሆን ሌሎች እንደነ ዶክተር ጌታቸው አይነቶች ናቸው አዝለው ሊገቡ

የሚፈልጉት። አንድ ሰሞን አቋሙን ቀይሯል ብለው ማስወራትም ጀምረው ነበር። ያም ቢሆን በተደጋጋሚ ተጋልጧል።

እዚህ ላይ ሁላችንም የምንደሰተው በእርግጥም ይህ ድርጅት ትልቁን የማህበረሰባችን ክፍል እወክላለሁ ሲል እንደ አናሳ እለያለሁ በማለት ሳይሆን፣ እንደትልቅ ከሌሎች ጋር በመቆም ነው። ኦነግ የሚያስበው እንደትንሽ በመሆኑ በምንም መልክ የኦሮሞኛ ተናጋሪ የሆነውን አይወክልም። ቢሆንማ ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ አንድነት ብሎ ከሁሉም በፊት በተነሳ። ዶክተር ጌታቸው ከብሔራዊ ድርጅት ዝቅ ብለው ኦነግን ደግፉ ሲሉ በማፈር አይ እንዳማሩ አይሞቱ የሚለውን አስታውሷል፤ ላየ ለሰማ ሁሉ።

ቸር ይግጠመን